የማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል መንግሥት ፍትህ ቢሮ
Central Ethiopia Region State Justice Bureau


ቁጥር. 02-25/5265
ቀን. 05/ቢ/2017

# ለማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል ሳይንስ እና ኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ቢሮ

**ወራቤ**

ጉዳዩ፡- <u>የተመዘገበ መመሪያ መላክን ይመለከታል</u>

ከመግቢያው ለመግለጽ እንደተሞከረው ቢሮችሁ በቁጥር ማ/ኢ/ሳ/ኢ/ቴ/ቢ.0078/01/11-112 በቀን 21/04/2017 ዓ/ም በተጻፈ ደብዳቤ ከዚህ ቀደም ሲጠቀምበት የነበረውን የሳይንስ ቴክኖሎጂ እና ኢኖቬሽን ማበረታቻ እና ሽልማት አሰጣጥ መመሪያን እንዲመዘገብልን በማለት መጠየቃችሁ ይታወቃል፡፡

በዚህ መሰረት ከተቋማችሁ የመጣውን መመሪያ በጥልቀት ፈትሸን በማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል መንግስት የአስተዳደር ሥነ ስርአት አዋጅ ቁጥር 23/2016 አንቀጽ 16/2/ መሰረት በዛሬው ቀን ማለትም ጥር 5/2017 ዓ/ም " **የማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል መንግስት ሳይንስ እና ኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ቢሮ ያወጣውን የሳይንስ እና ቴክኖሎጂ ኢኖቬሽን ማበረታቻ እና ሽልማት አሰጣጥ መመሪያ ቁጥር 06/2017 ዓ.ም** "ሆኖ የተመዘገበ መሆኑን እየገለጽን በክልሉ የአስተዳደር ሥነስርአት አዋጅ ቁጥር 23/2016 አንቀጽ 17/4/ መሰረት ተቋማችሁ መመሪያውን ተደራሽ ለማድረግ እንዲቻል ለተጠቃሚዎች በመመሪያው ይዘት ላይ ግንዛቤ የማስጨበጥ ስራ እንዲሰራ !መሪያው ስካን ተደርጎ በፒዲኤፍ ፎርማት በቢሮችሁ ድረ ገጽ ላይ እንዲጫን እንዲሁም መመሪያውን በማሳተም ለሚመለከታቸው መንግስታዊ እና ሌሎች ባለድርሻ አካላት እንዲሰራጭ ወይም ማንኛውም የመመሪያ ቅጅ ማግኘት ለሚፈልግ ሰው መመሪያውን ባለበት ሁኔታ የመመልከት ወይም ወጪውን ሸፍኖ ከቢሮችሁ እንዲያገኝ እንዲደረግ እያሳሰብን <u>21</u> ገጽ የያዘውን መመሪያ በዚህ ደብዳቤ ሸኝነት የላክን መሆናችንን እንገልፃለን፡፡

<u>ግልባጭ</u>

- ለቢሮ ኃላፊ ጽ/ቤት
- ለህግ ጉዳዮች ዘርፍ
- ለህግ ጥ/ማ/ማ/ ዳይሬክቶሬት

አህመዲን ሶማ
...medin Soma
...ሮ ኃላፊ
... Justice Bureau


ፖ/ሳ የመ.ሣ.ቁ 291 P.O. Box
ስ.ቁ 046 220 58 00 Tel
ፋክስ 046 221 24 37 Fax
emal:- justicebureauplan@gmail.com


ፍትህ ለሁሉም!!!Justice for All!!!

በማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል መንግሥት የሳይንስና ኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ቢሮ
Central Ethiopia *Regional State Science & Information Technology Bureau*

ቁጥር ማዕ/ሳኢ/ቴቢ/
ቀን 21 ---/---/2017 ዓ.ም

ለማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልላዊ መንግስት ፍትህ ቢሮ

ሀላባ

ጉዳዩ፡- <u>መመሪያ እንዲመዘገብልን ስለመላክ ይሆናል፣</u>

ከላይ በርዕሱ ለመግለጽ እንደተሞከረው ማዕካለዊ ኢትዮጲያ ክልል ሳይንስና ኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጅ ቢሮ ለስራ መተግበሪያ የሚሆን መመሪያ ማለትም "የሳይንስ፣ቴክኖሎጂና ኢኖቬሽን ማበረታቻና ሽልማት አሠጣጥ የአሠራር መመሪያ" በቀድሞ ደ/ብ/ብ/ህ/ክ/መንግስት የነበረዉን ወደ ማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል ቀይረን /አሻሽለን/ አዘጋጅተን ከቢሯችሁ የተሰጡትን አስተያየቶች አካተን በመኔጅመንት አጽድቀን የላክን መሆኑን እየገለጽን የማኔጅመንት ዉይይት ቃለ-ጉባኤ ከዚህ ሸኚ ደብዳቤ ጋር አባሪ አድርገን የላክን መሆኑን ጭምር እየገለጽን መመሪያዉ እንዲመዘገብልን እንጠይቃለን፡፡

/// ከሰላምታ ጋር ///

ግልባጭ

- ለቢሮ ኃላፊ
- ለሳይንስና ቴክኖሎጂ ፈጠራ ስርጸት ዘርፍ
- ለኢኮቴ ልማትና አስተዳር ዘርፍ
- ለቢሮ ኃላፊ አማካሪ

<u>ሳኢቴቢ፤</u>

Tele:- 046-771-08-49
- 046-771-07-92
- 046-771-49-63
Facebook : - www.facebook.com Science and Information Technology Bureau
Website:-www.sirtda.gov.et Email : - snnprsita02@gmail.com https://10.208.215.9/owa
Telegram:- *Science and Information Technology Bureau*

# የማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል መንግስት ማዕከላዊ ነጋሪት ጋዜጣ

# MAEKELAWI NEGARIT GAZETA OF THE CENTRAL ETHIOPIA REGIONAL STATE

## የማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል መንግስት ሳይንስና ኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ቢሮ

## Central Ethiopia Regional State,Bureau Of Science and Information Technology

| ወራቤ 2ኛ ዓመት ቁጥር--<br>ታህሳስ____ 2017 ዓ.ም | በማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ | Worabe 2nd Year No--<br>December _/2024 |
|---|---|---|


# የማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል መንግስት የሳይንስ፣ቴክኖሎጂና ኢኖቬሽን ማበረታቻና ሽልማት አሠጣጥ የአሠራር መመሪያ ቁጥር 06/2017

<u>መግቢያ</u>

በክልሉ የሚገኙ የሳይንስና ቴክኖሎጂ እና የፈጠራ ስራ ተዋናዮችን ለማበረታታት የሚያስችል የአሰራር ስርዓት በማስፈን እና የዉድድር መንፈስ በመፍጠር በክልል ደረጃ የቴክኖሎጂ ዉጤቶች የመማር፤የመጠቀም፤የመቅዳት፤የማሻሻል እና የመፍጠር አቅም የሚገነባበትን ምቹ ሁኔታ መፍጠር አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤ የማእከላዊ ኢትዮጵያ ክልል ሳይንስና ኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ቢሮ በክልሉ የአስፈጻሚ አካላት አዋጅ ቁጥር 199/2015 አንቀጽ 39 ንኡስ አንቀጽ 2 መሰረት መመሪያ አውጥቷል።

## ክፍል አንድ

## ጠቅላላ ድንጋጌዎች

### 1. አጭር ርዕስ

ይህ መመሪያ ሳይንስና ኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ቢሮ የሳይንስ፣ ቴክኖሎጂና ኢኖቬሽን ማበረታቻና ሽልማት አሠጣጥ የአሠራር መመሪያ ቁጥር - - -/2017 ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

### 2. ትርጓሜ

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ መመሪያ ፦

1. **"ሳይንስ"** ማለት ነባራዊውን አለም እና የተፈጥሮ ህግጋትንና ክስተቶችን ለማብራራትና ለመገንዘብ የሚያስችለንን ዕውቀት በምልከታና በሙከራ የምናገኝበት ዘዴ ነው፤
2. **"ቴክኖሎጂ"** ማለት ሳይንሳዊ ዕዉቀትን ተግባራዊ በማድረግ የሚገኝ እና የተወዳዳሪነት እና የማድረግ አቅም የሚያሻሽል ማንኛዉም አሰራር፣አደረጃጀት፣ስርዓት ወይም ቁስ ማለት ነው።
3. **"ኢኖቬሽን"** ማለት የተፈጠረ ቴክኖሎጂን የሚያሻሽል፣ለነበረ ቴክኖሎጂ አዲስ የጥሬ ዕቃ ምንጭ ወይም አዲስ ገበያ የማስገኘት ወይም የተቀላጠፈ ወይም በዚሁ የማሻሻል ሥራ የተነሳ የማምረቻ ወይም የአገልግሎት ጊዜንና ወጪን የሚቀንስ ወይም ገበያን የሚያሰፋ ቴክኒካል የመፍትሄ ሃሳብ ነው።
4. **"ትድኝት ማዕከል"** ማለት የተለያዩ ት/ቤቶችን በመረብ የሚያገናኝና የልምድ ልውውጥ የሚያሳዩበት ማዕከል ነው።
5. **"የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት"** ማለት ከ5ኛ እስከ 8ኛ ክፍል ያለው የትምህርት ደረጃ ነው።
6. **"የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት"** ማለት ከ9ኛ እስከ 12ኛ ክፍል ያለው የአጠቃላይ የትምህርት ደረጃ ነው።
7. **"አጠቃላይ ትምህርት"** ማለት በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (5) እና (6) ላይ የተጠቀሱትን የመጀመሪያና የሁለተኛ ደረጃ ትምህርትን የሚያጠቃልል ነው።
8. **"ተቋም"** ማለት የፈጠራ ስራቸውን ይዘው የቀረቡ የግል ወይም የመንግስት አምራች ወይም አገልግሎት ሰጪ ተወዳዳሪ ተቋማት ነው።
9. **"ግለሰብ የፈጠራ ባለሙያ"** ማለት የፈጠራ ወይም የምርምር ውጤትን በግል ሰርተው የሚቀርቡ ተወዳዳሪዎች ማለት ነው።
10. **"ክልል"** ማለት የማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል ነው።
11. **"ቢሮ"** ማለት በማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል ሳይንስና ኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ቢሮ ነው።

12. "ትምህርት ቢሮ" ማለት በማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል ትምህርት ቢሮ ነው።

13. "ዩኒቨርሲቲ" ማለት በክልሉ ውስጥ የሚገኙ ሀገር አቀፍ ከፍተኛ የትምህር ተቋማት ነው።

14. "ሽልማት" ማለት ቢሮ በሚዘጋጅ የሳይንስና ቴክኖሎጂ ፈጠራ ውጤት ስራ ባለቤቶች ውድድር የላቀ ውጤት ለሚያስመዘግቡ ተወዳዳሪዎች የሚሰጥ የእውቅና ምስክር ወረቀት፣ሜዳሊያና የገንዘብ ወይም የአይነት ሽልማት ነው።

15. "ገምጋሚና መራጭ ኮሚቴ"ማለት በዚህ መመሪያ መሠረት የሚደራጅ የተወዳዳሪዎችን የቴክኖሎጂ ፈጠራ ውጤት ስራ በማወዳደሪያ መስፈርቶች መሰረት በመገምገም አሸናፊዎችን ለይቶ ለቢሮ ኃላፊ የሚያቀርብ ኮሚቴ ነው።

16. "ቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ" ማለት ማለት በውድድሩ በገምጋሚና መራጭ ኮሚቴው በተሰጠው ውጤት የማይስማሙ አመልካቾችን ቅሬታ ተቀብሎ የውጤት አሰጣጥ ሂደቱን አጣርቶ የውሳኔ ሀሳብ ለቢሮ ኃላፊ የሚያቀርብ ኮሚቴ ነው፡

17. በዚህ መመሪያ በወንድ ጾታ የተገለጸ አነጋገር ሴትንም ይጨምራል።

3. ዓላማዎች

1. በክልሉ የልማት የትኩረት ዘርፎች ፍላጎትን መሠረት ያደረጉና ችግር ፈቺ የሆኑ የምርምርና የቴክኖሎጂ ፈጠራ ውጤት ባለቤት ለሆኑ ባለሙያዎችና ተቋማት እውቅናና ማበረታቻ ለመስጠት፤
2. በምርት፣ በአሰራር እና በአደረጃጀት የላቀ የምርምርና የቴክኖሎጂ ልማትና ፈጠራ ተግባራትን ያከናወኑ ግለሰቦችንና ተቋማት ዕውቅና በመስጠት በክልሉ የማምረቻና አገልግሎት ሰጪ ኢንዱስትሪዎች የምርምርና የቴክኖሎጂ በመማርና አጠቃቀም ረገድ የሚያደርጉትን አስተዋጽኦ ማሳደግ፤
3. የክልሉ ማህበረሰብ በሳይንስና ቴክኖሎጂ ተግባራት ተሳታፊ እንዲሆንና ቴክኖሎጂ የመጠቀም ባህሉን የማዳበር ተነሳሽነት እንዲጎለብት ለማድረግ ፤
4. መንግስት ለትምህርት መሻሻል ያስቀመጠውን የትኩረት አቅጣጫ 70/30 በመደገፍ ተማሪዎች በንድፈ ሀሳብ የተማሩትን ወደ ተግባር በመቀየር የሚሰሩትን የተለያዩ የፈጠራ ስራዎች ለማበረታታት፤
5. በፈጠራ ስራቸውና በሙያቸው አርአያ የሆኑ የሳይንስና የሂሳብ መምህራንን እውቅናና ማበረታቻ መስጠት ነው።

4. የመመሪያው ተፈጻሚነት ወሰን

ይህ መመሪያ፣

1. በክልሉ ውስጥ ባሉ ሁሉም ዞኖችና ልዩ ወረዳዎች በሚገኙ የመንግስትና የግል የመጀመሪያና ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች፣በመደበኛ የትምህርት መርሐ

ግብር በሚያስተምሩና በሚማሩ እና የፈጠራ ስራቸውን በሚያቀርቡ ተወዳዳሪ ኢትዮጵያዊያን የሳይንስና የሒሳብ መምህራንና ተማሪዎች፣ የቴክኒክና ሙያ ት/ስልጠና ኮሌጅ አሰልጣኝና ሰልጣኞች፣ የዩኒቨርሲቲ መምህራንና ተማሪዎች፤

2. በክልሉ የተለዩ የትኩረት ዘርፎች ማለትም በግብርና፣ በኢንፎርሜሽንና ኮሙኒኬሽን ቴክኖሎጂ፣ በማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪ፣ በቱሪዝም እና በማዕድንና ኢነርጂ እንዲሁም ሌሎችም ላይ ችግር ፈቺ የምርምርና የቴክኖሎጂ ፈጠራ ባለቤት በሆኑ ግለሰቦችና ተቋማት ላይ በሙሉ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

## ክፍል ሁለት

## የሽልማት ምድቦች፣ ተወዳዳሪዎች ማሟላት የሚገባቸው ቅድመ ሁኔታዎች እና መምረጫ መስፈርቶች

### 5. የሽልማት ምድቦች

በዚህ መመሪያ መሠረት የፈጠራ ሥራን ለማበረታታት ለፈጠራ ስራ ባለቤቶች እንዲሁም ለመምህራንና ተማሪዎች የሚሰጠው ሽልማት ከዚህ በታች የተዘረዘሩት ስድስት ምድቦች ይኖሩታል፡፡

1. የፈጠራ ስራ ባለቤት ተቋማት ምድብ
2. የፈጠራ ስራ ባለቤት ግለሰቦች ምድብ
3. የፈጠራ ስራ ባለቤት ሴቶች ምድብ
4. የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት የመምህራንና ተማሪዎች ሽልማት ምድብ
5. የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት የመምህራንና ተማሪዎች ሽልማት ምድብ
6. የመጀመሪያና ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት የሴት ተማሪዎች ምድብ፤
7. የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ተማሪዎች ምድብ፤
8. የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት መምህራን ምድብ፤
9. እንደ አስፈላጊነቱ ሌሎች ተጨማሪ ምድቦችም ሊካተቱ ይችላሉ፡፡

### 6. የፈጠራ ባለቤቶች ተወዳዳሪዎች ማሟላት የሚገባቸው ቅድመ ሁኔታዎች

በዚህ መመሪያ መሰረት ለሽልማት የሚቀርቡ ዕጩ ተወዳዳሪዎች ፡-

1. በክልሉ የሚኖር ኢትዮጵያዊ ወይም በክልሉ የሚኖሩ ኢትዮጵያዊያን አባላት ያሉት ቡድን ወይም በክልሉ ተመዝግቦና ህጋዊ ዕውቅና አግኝቶ እየሰራ የሚገኝ ተቋም፤
2. የፈጠራ ውጤቱ በሳይንስና ቴክኖሎጂ ዙሪያ የሆነ፤
3. የፈጠራ ውጤቱ ከአዕምሯዊ ንብረት ጥበቃ መስሪያ ቤት በሌላ ግለሰብ ያልተመዘገበ ወይም ከተቋሙ የበላይ ኃላፊ የተጻፈ የፈጠራ ባለቤትነቱን የሚያረጋግጥ ህጋዊ ደብዳቤ ማቅረብ የሚችል፤

4. ለውድድር የሚቀርበው የፈጠራ ውጤት ለተጠቃሚው ተላልፎ ችግር ፈቺነቱ በተጨባጭ የተረጋገጠና ተግባራዊነቱ በሚመለከተው አካል ህጋዊ ማረጋገጫ የተሰጠው፤
5. ከዚህ ቀደም በክልሉ ሳይንስና ኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ቢሮ ወይም በፌዴራል ኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር በተዘጋጀ ተመሳሳይ ውድድር ቀርቦ አሸናፊ ያልሆነ የፈጠራ ወይም የምርምር ውጤት፤
6. የሚቀርበው የምርምር ወይም የፈጠራ ውጤት ሰነድ መነሻ ችግሩን ፣የምርምር ስነ-ዘዴ፣ ወሰኑን፣ ፈጠራው ያስገኘውን ዕውቀትና ቴክኖሎጂው አሁን በስራ ላይ ከሚገኘው አሠራር በተሻለ የሚያስገኘው ጠቀሜታዎችን በግልጽ የሚያብራራ ይዘት ያለው ዶክመንት በሶፍት ኮፒና በሀርድ ኮፒ ማቅረብ የሚችል፤
7. ተወዳዳሪ ግለሰቡ ወይም ቡድኑ ወይም ተቋሙ በምርምር ዲስፕሊን ጥሰት ጥያቄ የማይቀርብበት መሆን ይኖርበታል።

## 7. የመደበኛ ትምህርት መምህራንና ተማሪዎች ለውድድሩ ማሟላት የሚገባቸው ቅድመ ሁኔታዎች

በዚህ መመሪያ መሰረት ለሽልማት የሚቀርቡ ዕጩ ተወዳዳሪዎች ፡-

1. በመደበኛ ትምህርት መርሀ ግብር ሙሉ ጊዜያቸውን በሳይንስና ሂሳብ ትምህርቶች በመምህርነት የሚያገለግሉ ኢትዮጵያዊያን መምህራን፤
2. በመደበኛ ትምህርት መርሀ ግብር የሳይንስና ሂሳብ ትምህርት የሚማሩ ኢትዮጵያዊያን ተማሪዎች፤
3. ከዚህ ቀደም የተሸለሙ መምህራንም ሆኑ ተማሪዎች በተጫይ ውድድር የሚቀርቡት ከዚህ በፊት በተሸለሙበት ስራዎች ሳይሆን በሌላ አዲስ ስራዎች ከሆነ፤
4. ለውድድር የሚቀርቡ የዕጩ ተወዳዳሪዎች የፈጠራ ሞዴሎችና ናሙናዎች በተወዳዳሪው ግለሰብ የተሰሩ ከሆነ፤
5. ለውድድር የሚቀርቡ ስራዎች መረጃ በሰነድ፣ በፎቶ፣ በተንቀሳቃሽ ምስል ወይም በሌላ አስፈላጊ በሆኑ የማቅረቢያ ዘዴዎች የተደገፉ መሆን ይኖርባቸዋል።
6. ከአንድ ትምህርት ቤት የሚቀርቡ ዕጩ ተወዳዳሪዎች በተመሳሳይ ስራ ለውድድር መቅረብ አይችሉም።

8. መምረጫ መስፈርቶች

የተወዳዳሪዎች የውድድር ውጤት ከዚህ መመሪያ ጋር አባሪ ተደርጎ በቀረበው የውድድር መስፈርቶችና ክብደታቸው መሰረት በተሠጡ ነጥብ መነሻነት የሚሰላ ይሆናል

## ክፍል ሶስት

## የሽልማቱ ዓይነት ፣ የሽልማት አስተዳደርና የክትትል ስርዓት

9. የሽልማቱ ዓይነት

በየምድቡ ተወዳድረው አሸናፊ የሚሆኑ ተወዳዳሪዎች በደረጃቸው መሰረት የዕውቅና የምስክር ወረቀት፣ ሜዳሊያና የገንዘብ ሽልማት የሚያገኙ ሆኖ የገንዘብ ሽልማት መጠኑ በየውድድሩ ወቅት በቢሮው የሚገለጽ ይሆናል። በተጨማሪም የተመረጡ የተሸላሚዎች የፈጠራ ስራዎች በክልል አቀፍ ደረጃ በሚዘጋጅ የሳይንስና ኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ኤግዚቢሽኖች ለህብረተሰቡ እንዲያቀርቡ የሚደረግ ሲሆን ምርታቸውን ለማህበረሰቡ በማድረስ የኢኮኖሚ ተጠቃሚ የሚሆኑበት ሁኔታ ሊመቻች ይችላል።

10.የሽልማት አስተዳደርና የክትትል ስርዓት

ሽልማቱን የሚያስተዳድረው ቢሮው ሲሆን የትምህርት ቢሮ እና የሴቶችና ህጻናት ጉዳይ ቢሮ ክትትል የሚያደርጉ ይሆናል።

## ክፍል አራት

## ኮሚቴዎችን ስለማቋቋም

11.የፈጠራ ባለቤት ተወዳዳሪዎች የሽልማት ገምጋሚና መራጭ ኮሚቴ ስለማቋቋም

1. በክልሉ ከሚገኙ ዩንቨርሲቲዎች የተዉጣጡ የሳይንስና ቴክኖሎጂ ባለሙያዎች፣ ከተለያዩ የሳይንስና ቴክኖሎጂ ምርምር ተቋማትና ሴክተር መ/ቤቶች የሚወክሉ አባላት ያሉት ክልል አቀፍ ገምጋሚና መራጭ ኮሚቴ የሚቋቋም ሲሆን የሚከተሉት አባላት ይኖሩታል።

ሀ/ የልማት መሪ መስሪያ ቤቶች

ለ/ በክልሉ ከሚገኙ ዩኒቨርሲቲዎች የቴክኖሎጂ ኢንስቲትዩት/ፋኩልቲ

ሐ/ በቢሮው የሚወክሉ ሁለት አባላት

መ/ እንደ አስፈላጊነቱ ሌሎች አባላትን በማሳተፍ ሊደራጅ ይችላል።

2. ሰብሳቢና ምክትል ሰብሳቢ ከአባላቱ መካከል በአባላቱ ይመረጣል።

3. የቢሮው ተወካይ ከሆኑት አባላት መካከል አንደኛው የኮሚቴው ጸሐፊ በመሆን ያገለግላል።

## 12.የመደበኛ ትምህርት መምህራንና ተማሪዎች የሽልማት ገምጋሚና መራጭ ኮሚቴ ስለማቋቋም

1. በክልል ደረጃ የተወዳዳሪዎችን የፈጠራ ስራ መረጣ በበላይነት የሚያስፈጽም ክልል አቀፍ የሽልማት ገምጋሚና መራጭ ኮሚቴ ይቋቋማል፡፡
2. ኮሚቴው የሚከተሉት አባላት ይኖሩታል፡-

ሀ/ የቢሮው ተወካይ (ሰብሳቢ)

ለ/ የትምህርት ቢሮ ተወካይ (ጸሀፊ)

ሐ/ የሴቶችና ህጻናት ጉዳይ ቢሮ ተወካይ (አባል)

መ/ እንደ አስፈላጊነቱ ከሙያው ጋር ተያያዥነት ካላቸው አጋር ተቋማትና የሳይንስና ቴክኖሎጂ የሙያ ማህበራት የሚወከሉ አባላት ይኖሩታል፡፡

## 13.የቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ

1. ቢሮው የቅሬታ ሰሚ ኮሚቴውን ያቋቁማል፡፡
2. የቅሬታ ሰሚ ኮሚቴው ከ7 (ሰባት) ያልበለጡ አባላት እንዲኖሩት ሆኖ የሚደራጅ ሲሆን የሚከተሉትን አካላት በማሳተፍ ይዋቀራል፡-

ሀ/ የሳ/ቴ/አቅም ግንባታ ዳ/ዳይሬክተር ............... ሰብሳቢ

ለ/ ከኢኮቴ ዘርፍ የሚወከል አንድ ሰው ............... ጸሐፊ

ሐ/ የቢሮው ስነ-ምግባር መከታተያ ክፍል መኮንን ......... አባል

መ/ የትምህርት ቢሮ ተወካይ ......... አባል

ሠ/ የሴቶችና ህጻናት ጉዳዮች ቢሮ ተወካይ ......... አባል

ረ/ እንደ አስፈላጊነቱ ሌሎች አባላትን ሊያካትት ይችላል

## ክፍል አምስት

## ተግባርና ኃላፊነት

## 14.የቢሮው ተግባርና ኃላፊነት

1. የዉድድር ማስፈጸሚያ መመሪያ ያዘጋጃል አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ መመሪያዉን ያሻሽላል፤
2. የዉድድሩን ማስፈጸሚያ ዕቅድ ያዘጋጃል ፤ የሽልማት በጀት ያስመድባል፤
3. ጉዳዩ የሚመለከታቸውን ሴክተር መ/ቤቶች ያስተባብራል፤
4. የውድድር መርሃ ግብር ያዘጋጃል፤
5. የተወዳዳሪዎችን ጥሪ በተለያዩ የመገናኛ አማራጮች ያስተላልፋል ፤አስፈላጊውን መረጃ ይሰጣል፤
6. የተወዳዳሪዎችን ምዝገባ ያከናውናል፤

7. እንደ አስፈላጊነቱ ከዞን፣ ከልዩ ወረዳ፣ ወረዳና ከተማ አስተዳደር ጋር ግንኙነት ይፈጥራል፤
8. የሽልማት አፈጻጸሙን በአካል በመገኘትና በሌላ መንገድ ይከታተላል፤
9. የተሸላሚዎችን መረጃ ያደራጃል፤
10. ክልላዊ የሽልማት ስነ ስርዓት ያካሄዳል።

**15.የትምህርት ቢሮ ተግባርና ኃላፊነት**

1. ከቢሮው ጋር በመሆን የሽልማት ስነ ስርዓት ዕቅድና መርሀ ግብር ያዘጋጃል፤
2. ዞኖችና ልዩ ወረዳዎች ዕጩ ተወዳዳሪዎቻቸው የፈጠራ ስራቸውን ከድጋፍ ሰጪ መረጃዎች ጋር አያይዘው በወቅቱ እንዲያቀርቡ ያደርጋል።
3. በሚደራጁ ኮሚቴዎች ይሳተፋል።

**16.የዩንቨርሲቲዎች ተግባርና ኃላፊነት**

1. ከቢሮው ጋር በመሆን የሽልማት ስነ ስርዓት ዕቅድና መርሀ ግብር ያዘጋጃሉ፤
2. በተዘጋጀዉ መመሪያ መሰረት መስፈርቱን በማሟላት በሳይንስና ቴክኖሎጂ የፈጠራ ስራ ላይ የተሳተፉ መምህራንና ተማሪዎችን በማወዳደር እና በየምድቡ ከ1-3 የወጡትን በመለየት ሙሉ ሰነዱ ለቢሮው የሚቀርብበትን ሁኔታ ያመቻቻሉ።

**17. የመደበኛ ትምህርት መምህራንና ተማሪዎች ገምጋሚና መራጭ ኮሚቴ ተግባርና ኃላፊነት**

1. ከዞንና ከልዩ ወረዳዎች የሚቀርቡ ዕጩዎችን ውጤት ትክክለኛነት ያረጋግጣል፤
2. በተወዳዳሪዎች የተሰሩ ስራዎችን በመስፈርቶቹ መሠረት በመገምገም ውጤት ይሰጣል፤
3. ለሽልማት ብቁ የሆኑትን ተወዳዳሪዎች ምርጫ በመምረጥና በየደረጃቸው በማስቀመጥ የውሳኔ ሀሳብ ለቢሮ ኃላፊ ያቀርባል።

**18.የፈጠራ ባለቤቶች ተወዳዳሪዎች የሽልማት ገምጋሚና መራጭ ኮሚቴ ተግባርና ኃላፊነት**

1. ለውድድር የቀረቡ የምርምርና የቴክኖሎጂ ስራዎችን በዚህ መመሪያ ተያይዞ በተቀመጠው መስፈርት መሰረት መዝኖ ውጤት ይሰጣል፤
2. የውድድሩን ውጤት ለቢሮው አቅርቦ እንዲጸድቅ ያደርጋል፤
3. ይህንን መመሪያ በማሻሻል ሒደት ግብዓት የሚሆኑ ሀሳቦችን ያቀርባል።

**19.የሰብሳቢ ተግባርና ኃላፊነት**

1. የኮሚቴውን ተግባር በበላይነት ይመራል፤
2. የኮሚቴውን ተግባራት አስመልክቶ ዝርዝር መርሐ ግብር ከአባላቱ ጋር ሆኖ በማዘጋጀት ለቢሮ ኃላፊው አቅርቦ ያስጸድቃል፤
3. ሌሎች አባላት የሚያከናውኑትን ሙያዊ ተግባራት ያከናውናል።

4. የገምጋሚና መራጭ ኮሚቴው ሰብሳቢ የተጠቃለለ የውድድር ውጤት ለቢሮው በማቅረብ ያስጸድቃል፡፡

**20.የኮሚቴው ምክትል ሰብሳቢ ተግባርና ኃላፊነት**

የፈጠራ ባለቤት ተወዳዳሪዎች የሽልማት ገምጋሚና መራጭ ኮሚቴ ምክትል ሰብሳቢ የሚከተሉት ተግባርና ኃላፊነቶች ይኖሩታል ፡-

1. ሌሎች አባላት የሚያከናውኑትንሙያዊ ተግባራት ያከናውናል፤
2. ሰብሳቢው በማይኖርበት ማንኛውም አጋጣሚ ኮሚቴውን የመምራትና ሌሎች የሰብሳቢውን ተግባራት ያከናውናል፡፡

**21.የኮሚቴው ጸሐፊ ተግባርና ኃላፊነት**

የፈጠራ ባለቤት ተወዳዳሪዎች የሽልማት ገምጋሚና መራጭ ኮሚቴ ጸሐፊ የሚከተሉት ተግባርና ኃላፊነቶች ይኖሩታል፡-

1. የተወዳዳሪዎችን የማመልከቻ ሰነዶች ከተቀመጡ መስፈርቶች አንጻር በማጣራት ለውድድሩ ብቁ የሆኑትን ተወዳዳሪዎች መረጃ አደራጅቶ ለገምጋሚና መራጭ ኮሚቴው ያቀርባል፤
2. የኮሚቴው ስራ ውጤታማና ቀልጣፋ ሆኖ እንዲፈጸም ሁኔታዎችን ያመቻቻል፤
3. ኮሚቴው የሚያወጣውን መርሐ ግብር መሠረት አድርጎ ለተወዳዳሪዎች የፈጠራ ስራ ማቅረቢያ ፕሮግራሙን ያሳውቃል፡፡

**22.የኮሚቴው አባላት ተግባርና ኃላፊነት**

ለውድድር የቀረቡትን ማመልከቻዎች በየሙያ መስመራቸው በተቀመጠው መስፈርት መሠረት እየገመገሙ ከኮሚቴው አባላት ጋር እየተወያዩ ውጤት ይሠጣሉ፡፡

## ክፍል ስድስት

**የተሸላሚዎች አመራረጥ ሂደት ፣ የቅሬታ አፈታት ስርዓት ፣ ክትትልና ግምገማ**

**23.የፈጠራ ባለቤት ተሸላሚዎች አመራረጥ ሂደት**

1. የውድድር ማስታወቂያው በክልሉ መገናኛ ብዙሃን፤ በሶሻል ሚዲያ፤ በደብዳቤ ጥሪ በማስተላለፍ ወዘተ እንደ አስፈላጊነቱ እና አፋጣኝነቱ ታይቶ ሊተላለፍ ይችላል፤
2. ቢሮው የማመልከቻ ቅጽ አሞላልና ሌሎች የውድድሩ ጉዳዮች ዙሪያ ለአመልካቾች አስፈላጊውን ማብራሪያ ይሰጣል፤
3. የተሟላ የማመልከቻ ቅጽ ከአዕምሯዊ ንብረት ባለቤትነት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት እንዲሁም ስለ የፈጠራና የቴክኖሎጂ ስራው በተጠቃሚዎች የተሠጠ ህጋዊ የፋይዳ ማረጋገጫ ደብዳቤ ጋር በማያያዝ መቅረብ ይኖርበታል፡፡

4. ተወዳዳሪዎች በተያዘላቸው ቀጠሮ በመገኘት የፈጠራ ስራቸውን አስመልክቶ በገምጋሚና መራጭ ኮሚቴው ፊት ቀርበው ገለጻና ማብራሪያ ያቀርባሉ፡፡
5. ለሽልማት የሚያበቃው ዝቅተኛ አማካይ ውጤት 50% ነው፡፡

## 24.የመደበኛ ትምህርት መምህራንና ተማሪ ተሸላሚዎች አመራረጥ ሂደት

1. ሁሉም ዕጩዎች የሚመረጡት ሒሳብና ሳይንስ ትምህርትን መሠረት በማድረግ ለሠሩት የፈጠራ ስራ ሞዴሎች/ናሙናዎች ሲሆን አግባብነት ያላቸው ሌሎች መመዘኛዎችም ታሳቢ ይደረጋሉ፤
2. የዕጩ ተሸላሚ መረጣው የሚጀመረው በከተማ ወይም በወረዳ አስተዳደር ከሚገኙ ት/ቤቶች ይሆናል፤
3. ሁለትና ከዚያ በላይ የሆኑ ወንድ ዕጩ ተወዳዳሪዎች ተመሳሳይ ውጤት ካገኙ አሸናፊው በዕጣ የሚለይ ሲሆን አንዳቸው አካል ጉዳተኛ ከሆኑ ቅድሚያ ይሠጣል፤
4. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 3 የተገለጸው እንደተጠበቀ ሆኖ የተለያየ ጾታ ያላቸው ተወዳዳሪዎች ተመሳሳይ ውጤት ካገኙ ለሴት ተወዳዳሪ ቅድሚያ ይሠጣል፤
5. ሁለትና ከዚያ በላይ የሆኑ ሴት ዕጩ ተወዳዳሪዎች ተመሳሳይ ውጤት ካገኙ ሁሉም ተወዳዳሪዎች ተሸላሚ ይሆናሉ፤
6. ሁሉም ዞንና ልዩ ወረዳ በሁሉም ምድቦች የተመረጡ ዕጩ ተወዳዳሪ ተሸላሚዎችን ስም ዝርዝር የኮሚቴውን ቃለ ጉባኤ፣ ዕጩዎቹ በየመስፈርቱ የሰሯቸውን ስራዎችና ደጋፊ መረጃዎችና ማስረጃዎች (የጥናት ሰነዶች፣ ፎቶዎችና ተንቀሳቃሽ ምስሎች) በማያያዝ በተማሪዎችና መምህራን ማጠቃለያ አባሪ ቅጽ ሞልተው ለክልል ይልካሉ፡፡

## 25.ውጤት ስለማሳወቅ

የገምጋሚና መራጭ ኮሚቴው ጸሐፊ የተወዳዳሪዎች ውጤት በቢሮው ኃላፊ ሲጸድቅ ለአሸናፊዎች በማሳወቅ በሽልማት ፕሮግራም ላይ እንዲገኙ ጥሪ ያደርጋል፡፡

## 26.የቅሬታ አቀራረብና አፈታት ስርዓት

1.በውድድሩ የገምጋሚና መራጭ ኮሚቴዎች በተሰጠው ውጤት የማይስማማ አመልካች የውድድሩ ውጤት ይፋ ከተደረገ በኋላ ባሉት አምስት ተከታታይ የስራ ቀናት ውስጥ ቅሬታውንና የሚፈልገውን ውሳኔ በመግለጽ በቢሮው ለሚቋቋመው የቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ በጽሁፍ ማቅረብ ይኖርበታል፤
2. የቅሬታ ሰሚ ኮሚቴው የቅሬታ ማቅረቢያ ጊዜ ካለፈ ቦኋላ የሚቀርቡ ቅሬታዎችን ውድቅ ያደርጋል፤

3. የቅሬታ ሰሚ ኮሚቴው ከቀረቡ ቅሬታዎች ጋር ተያያዥነት ያላቸውን አስፈላጊ መረጃዎች እንዲቀርብለት ጠይቆ ይመረምራል፤

4. የቅሬታ ሰሚ ኮሚቴው የውሳኔ ሀሳብ ለመስጠት እንዲረዳው የገምጋሚና መራጭ ኮሚቴውን አግኝቶ ማብራሪያ እንዲሠጠው ሊጠይቅ ይችላል፤

5. የቅሬታ ሰሚ ኮሚቴው የሚቀርብለትን ቅሬታዎች አጣርቶ የውሳኔ ሀሳቡን ከቀረበበት ቀን ጀምሮ ባሉት አስር ተከታታይ የስራ ቀናት ውሥጥ ለቢሮው ኃላፊ በጽሑፍ ሪፖርት ያቀርባል፤

6. የቢሮው ኃላፊ የቅሬታ ሰሚ ኮሚቴው ያቀረበለትን የውሳኔ ሀሳብ በመመልከትና ማስረጃዎችን በመመርመር የመጨረሻ ውሳኔ ያስተላልፋል።

18.ክትትልና ግምገማ

በየደረጃው የሚገኙ የሽልማት አስፈጻሚ አካላት የሽልማቱን አፈጻጸም በየጊዜው ይከታተላሉ፣ ይገመግማሉ እንዲሁም የተሸላሚዎችን መረጃ ይይዛሉ።

## ክፍል ሰባት

## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

19.መመሪያውን ስለማሻሻል

1. ይህንን የአሰራር መመሪያ ቢሮው እንዲሻሻል ባመነበት ጊዜ ሁሉ ሊያሻሽለው ወይም ሊለውጠው ይችላል።

2. በዚህ አንቀፅ የንዑስ አንቀፅ 1 ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ ቢሮው መመሪያው በተሻሻለ በማናቸውም ጊዜ ለፍትህ ቢሮ መመሪያው የተሻሻለ ስለመሆኑ በማሳወቅ ማስመዝገብና ቁጥር እንዲሰጥ ማድረግ አለበት።

20.መመሪያው የሚጸናበት ጊዜ

ይህ መመሪያ በክልሉ የሳይንስና ኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ቢሮ ጸድቆ በክልሉ ፍትህ ቢሮ ከተመዘገበበት ከጥር 5 ቀን 2017 ዓ.ም ጀምሮ ተፈጻሚ ይሆናል።

ሰላሙ አማዶ

በማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል መንግስት የሳይንስና ኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ቢሮ ኃላፊ

Central Ethiopia Regional State Science & Information Technology Bureau

አባሪ-1፦ የመወዳደሪያ መስፈርት በግል ወይም በቡድን ለሚወዳደሩ የፈጠራ ስራ ባለቤቶች /የቴክኒክና ሙያ ት/ስልጠና ተማሪዎች እና መምህራን፤የዩንቨርሲቲ ተማሪዎችና መምህራን እንዲሁም የግል የፈጠራ ስራባለቤቶች)

| ተ.ቁ | መስፈርት | ክብደት በመቶኛ | የተሠጠ ውጤት |
|---|---|---|---|
| 1 | ስራው ትኩረት በተሠጣቸው የልማት ዘርፎች የሚኖረው የችግር ፈቺነት አስተዋጽኦ | 25 | |
| | ► ምርታማነትን ከማሳደግ አንጻር (አገልግሎት አሰጣጥን ከማሳደግ አንጻር) | 13 | |
| | ► የውጭ ሀገር ምርትን በመተካት/ የውጭ ምንዛሪን ከማሳደግ አንጻር | 12 | |
| 2 | የስራው የተለየ ገጽታ | 20 | |
| | ► የደንበኞችን የመግዛት አቅም ያገናዘበ ከመሆን አንጻር | 5 | |
| | ► ለአጠቃቀም ምቹና ቀላል ከመሆን አንጻር | 5 | |
| | ► ብቃት/ ኢፊሸንሲ | 5 | |
| | ► ጥራት | 5 | |
| 3 | የስራው አስተዋጽኦ | 25 | |
| | ► ተገቢ የተፈጥሮ ሃብት አጠቃቀምን ከማጎልበት አንጻር | 5 | |
| | ► የቴክኖሎጂ አጠቃቀምን ከማጎልበት አንጻር | 5 | |
| | ► የሳይንሳዊና የቴክኖሎጂ ዕውቀት ተግባራዊነት | 5 | |
| | ► የህብረተሰቡን በተለይም የሴቶችን የስራ ጫና ከመቀነስ አንጻር | 5 | |
| | ► የአካል ጉዳተኞችን ተግዳሮት ከመፍታት አንጻር | 5 | |
| 4 | ስራው የሚኖረው የስርጭት መጠን፤የመባዛትና የቀጣይነት ሁኔታ | 12 | |
| | ► አገር አቀፍ | 4 | |
| | ► ክልል አቀፍ | 4 | |
| | ► በውስን አካባቢ /በኢንዱስትሪ/ ደረጃ | 4 | |
| 5 | ቴክኖሎጂዉ ለማሸጋገር የሚያስችል የሰነድ ዝግጅት | 18 | |
| | ► የተሟላ ዲዛይን ያለዉ ቴክኖሎጂ ስለመሆኑ | 6 | |
| | ► የአዋጭነት ትንተና የተከናወነለት ስለመሆኑ | 4 | |
| | ► የአጠቃቀም ማንዋል የተዘጋጀለት ስለመሆኑ | 4 | |
| | ► የጥገና ማንዋል የተዘጋጀለት ስለመሆኑ | 4 | |
| | አጠቃላይ ዉጤት | (___/100) | |

አባሪ 2፦ የተሻለ ቴክኖሎጂ የሚያሸጋግሩ ወይም የሚጠቀሙ ተቋማት ማወዳደሪያ መስፈርት

| ተ.ቁ | መስፈርት | ክብደት በመቶኛ | የተሰጠው ውጤት |
|---|---|---|---|
| 1 | ስራው ትኩረት በተሠጣቸው የልማት ዘርፎች የሚኖረው የችግር ፈቺነት አስተዋጽኦ | 50 | |
| | ማህበራዊ ጠቀሜታ<br>► የማህበረሰቡን የአኗኗር ሁኔታ የሚያሻሽል<br>► የስራ ዕድል የሚፈጥር<br>► የሴቶች እና የአካል ጉዳተኞችን ተጠቃሚነት የሚያረጋግጥ | 20 | |
| | ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ<br>► ከዉጭ የሚመጡ ምርቶችን መተካት<br>► ለዉጭ ገበያ ምርት ማቅረብ | 20 | |
| | የተፈጥሮ አካባቢን ደህንነት ከመጠበቅ አኳያ<br>► የተፈጥሮ ሃብትን ቀጣይ በሆነ መንገድ የሚጠቀም<br>► ለአካባቢ ደህንነት መጠበቅ የሚሰራ | 10 | |
| 2 | የተቋሙ (የኢንዱስትሪዉ) የቴክኖሎጂ አቅም | 25 | |
| | ► ቴክኖሎጂን የመቀበል አቅም | 5 | |
| | ► ቴክኖሎጂን የማላመድ አቅም | 5 | |
| | ► ቴክኖሎጂን በዘላቂነት የመጠቀም አቅም | 5 | |
| | ► ቴክኖሎጂን የማሻሻል ወይም የመፍጠር አቅም | 5 | |
| | ► ቴክኖሎጂ የማሸጋገር አቅም | 5 | |
| 3 | የአጠቃላይ ጥራት ስራ አመራርን በተቋሙ በተገቢዉ ተግባራዊ ያደረገ | 25 | |
| | ► ሂደትን መሰረት ያደረገ አሰራር | 4 | |
| | ► ደንበኛ ተኮር | 5 | |
| | ► አሳታፊ አሰራር ያለዉ | 4 | |
| | ► ቀጣይነት ያለዉ መሻሻል | 4 | |
| | ► ወጥነት ያለዉ ተቋማዊ አሰራር | 4 | |
| | ► ተቋማዊ የማበረታቻ እና የሽልማት ስርዓትን ባህል ያደረገ | 4 | |
| | አጠቃላይ ዉጤት | (___/100) | |

አባሪ 3 የመጀመሪያ ደረጃ ተማሪዎች የሽልማት መስፈርት

| ተ.ቁ | መስፈርት | ክብደት | የተሰጠው ውጤት |
|---|---|---|---|
| 1 | በት/ቤት የተሠሩ አዲስ የፈጠራ ስራዎች | 65 | |
| | የፈጠራ ሀሳብን ማመንጨትና በራስ ጥረት መተግበር | 30 | |
| | በትምህርት ማበልጸጊያ ማዕከል ውሥጥ የተደረገ ተሳትፎ (ሞዴል፣ ቻርትና ሌሎች የትምህርት መሳሪያዎችን መስራት) | 20 | |
| | የፈጠራ ሀሳቡን ጠቀሜታ በሚገባ መግለጽ | 15 | |
| 2 | ሽልማት በሚሰጥበት ዓመት የመጀመሪያ መንፈቅ ያስመዘገበው የሂሳብና የሳይንስ ትምህርቶች አማካይ ውጤት | 15 | |
| 3 | ከመማር ማስተማር ስራዎች በተጓዳኝ በት/ቤት ውስጥ የሚያደርገው ተሳትፎ | 6 | |
| | የተለያዩ ጽሑፎችን በማዘጋጀት ሳይንስን በት/ቤት ሚኒ ሚዲያ ማስተዋወቅ | 3 | |
| | በት/ቤቱ የሳይንስ ክበብ የሚያደርገው የነቃ ተሳትፎ | 3 | |
| 4 | በማጠናከሪያ ትምህርት ለመጠቀምና ዕውቀትን ለሌሎች ለማካፈል ያለው ፍላጎትና ተነሳሽነት | 9 | |
| | በማጠናከሪያ ትምህርት የሚያደርገው ተጨባጭ እስተዋጽኦና አጠቃቀም | 3 | |
| | በቡድን ጥናት ትምህርት የሚያደርገው ተጨባጭ አስተዋጽኦና አጠቃቀም | 3 | |
| | እውቀትና ክህሎትን ለሌሎች ማካፈልና ማብቃት | 3 | |
| 5 | ባህሪና ስነ ምግባር | 5 | |
| | ህግና ደንብን በሚገባ የሚያከብር | 3 | |
| | ለሌሎች ተማሪዎች አርአያ መሆን | 2 | |
| | የተወዳዳሪው የተጠቃለለ ውጤት ከ100 % | | |



### አባሪ 4 ለመጀመሪያ ደረጃ መምህራን የተዘጋጀ የሽልማት መስፈርት

| ተ.ቁ | መስፈርት | ክብደት | የተሰጠው ውጤት |
|---|---|---|---|
| 1 | **በት/ቤት የተሰራ አዳስ የፈጠራ ስራ** | 45 | |
| | የአካባቢንና ማህበረሰብ ችግሮችን በተጨባጭ የመፍታት አቅም | 15 | |
| | በአካባቢ የሚገኙ ቁሳቁስና ሀብትን ጥቅም ላይ ከማዋል አንጻር | 10 | |
| | የአካባቢ ብክለትን የማያስከትልና ለጥበቃ ያለው አስተዋጽኦ | 8 | |
| | ለውድድር የቀረቡ የፈጠራ ስራዎች ብዛት | 12 | |
| 2 | **ከትምህርት ጋር የተጣጣመ ተግባራዊና ውጤት ያለው ምርምር ማካሔድ** | 12 | |
| | ምርምር በማካሄድ የተዘጋጀ ደረጃውን የጠበቀ ሰነድ | 5 | |
| | የምርምር ውጤቱን ለት/ቤቱ አካላትና ለሌሎች አትርቦ ማስገምገም | 3 | |
| | የምርምር ውጤቱን ተግባራዊ በማድረግ ተጨባጭ ውጤት ማስገኘት | 4 | |
| 3 | **አጋዥ/ማጣቀሻ (የቤተ ሙከራ ማኑዋል፣ሞጁል ወዘተ) ማዘጋጀት** | 8 | |
| | የተዘጋጁ ደረጃቸውን የጠበቁ የማጣቀሻ መጻህፍት | 4 | |
| | የተዘጋጁ ሞጁሎች | 2 | |
| | ወቅታዊነትን የጠበቀ የቤተ ሙከራ ማኑዋል | 2 | |
| 4 | **ሽልማቱ በሚሰጥበት ዓመትና ከዚያ ቀደም ባለው አንድ ዓመት በትምህርት ማበልጸጊያ ማዕከል ወይም በሌላ ቦታ የተዘጋጀ ከሚያስተምረው ትምህርት ጋር ተያያዥ የሆነ የማስተማሪያ መርጃ መሳሪያ ያዘጋጀ ስለመሆኑ** | 8 | |
| 5 | **የተማሪዎችን የመማር ፍላጎትና አቅም ለማጎልበት ያለው ተነሳሽነት** | 6 | |
| | የማጠናከሪያ ክፍል ማመቻቸት | 3 | |
| | በጉድኝት ማዕከል የሚያደርገው የላቀ ተሳትፎ | 3 | |
| 6 | **ንድፈ ሀሳብን ተግባራዊ ለማድረግ የቤተ ሙከራ አጠቃቀም** | 6 | |
| | የግል ዕውቀቱን ለማዳበር በቤተ ሙከራ የሚያደርገው ተሳትፎ | 3 | |
| | ተማሪዎቹን ለማስተማር ቤተ ሙከራን በተገቢ መጠቀም | 3 | |
| 7 | **ዕውቀት ፣ ክህሎትና የቋንቋ ችሎታ** | 5 | |
| | በሚያስተምረው ትምህርት ያለው ዕውቀት | 2 | |
| | የማስተማር ችሎታ | 2 | |
| | የቋንቋ ክህሎት | 1 | |
| 8 | **በትምህርት ቤቱ የሳይንስ ክበብ ያለው ተጨባጭ ተሳትፎ** | 5 | |
| | ክበቡን ለመመስረት ወይም ለማጠናከር ያደረገው ተጨባጭ ተሳትፎ | 1 | |
| | በክበቡ ያለው የማስተባበር ሚና | 2 | |
| | በክበቡ ያለው ንቁ ተሳትፎ | 2 | |
| 9 | **የተማሪዎች አያያዝና በት/ቤቱ የሚያሳየው አርአያነት** | 5 | |

| | | | |
|---|---|---|---|
| | ተገቢ የተማሪዎች አያያዝ የሚያደርግ መሆኑ | 3 | |
| | በት/ቤቱ የሚያሳየው አርአያነት | 2 | |
| | **የተወዳዳሪው የተጠቃለለ ውጤት ከ100 %** | | |

## አባሪ 5 የሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ተማሪዎች የሽልማት መስፈርት

| ተ.ቁ | መስፈርት | ክብደት | የተሰጠው ውጤት |
|---|---|---|---|
| 1 | ተግባራዊ የፈጠራ ስራና ተቀባይነት ያለው ጠቀሜታ | 55 | |
| | ተግባራዊ ሊሆን የሚችል የፈጠራ ሃሳብ ማመንጨት | 20 | |
| | የፈጠራ ሃሳብን በንድፍ ማሳየት | 15 | |
| | ንድፍን በተግባር (ናሙና ወይም ሞዴል) በመስራት ማሳየት | 20 | |
| 2 | ሽልማት በሚሰጥበት ዓመት የመጀመሪያ መንፈቅ ያስመዘገበው የሂሳብና የሳይንስ ትምህርቶች አማካይ ውጤት | 15 | |
| 3 | ንድፈ ሀሳብን ወደ ተግባር በመቀየር የተደረገ ተጨባጭ ጥረት | 10 | |
| | በቤተ ሙከራ የተሰሩ ስራዎች | 5 | |
| | በትምህርት ማበልጸጊያ ማዕከል የተሰሩ የትምህርት መርጃ መሳሪያዎች | 5 | |
| 4 | ከመማር ማስተማር ስራዎች በተጓዳኝ በት/ቤት ውስጥ የሚያደርገው ተሳትፎ | 6 | |
| | የተለያዩ ጽሑፎችን በማዘጋጀት ሳይንስን በት/ቤት ሚኒ ሚዲያ ማስተዋወቅ | 3 | |
| | በት/ቤቱ የሳይንስ ክበብ የሚያደርገው የነቃ ተሳትፎ | 3 | |
| 5 | በማጠናከሪያ ትምህርት ለመጠቀምና ዕውቀትን ለሌሎች ለማካፈል ያለው ፍላጎትና ተነሳሽነት | 9 | |
| | በማጠናከሪያ ትምህርት የሚያደርገው ተጨባጭ አስተዋጽኦና አጠቃቀም | 3 | |
| | በቡድን ጥናት የሚያደርገው ተጨባጭ አስተዋጽኦና አጠቃቀም | 3 | |
| | እውቀትና ክህሎትን ለሌሎች ማካፈልና ማብቃት | 3 | |
| 6 | ባህሪና ስነ ምግባር | 5 | |
| | ህግና ደንብን መጠበቅና ማክበር | 3 | |
| | ከደባል ሱስና አጉል ልማድ የጸዳ መሆን | 2 | |
| የተወዳዳሪው የተጠቃለለ ውጤት ከ100% | | | |

## አባሪ 6 ለሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት መምህራን የተዘጋጀ የሽልማት መስፈርት

| ተ.ቁ | መስፈርት | ክብደት | ውጤት |
|---|---|---|---|
| 1 | በት/ቤት የተሰራ አዳስ የፈጠራ ስራ | 45 | |
| | የአካባቢንና ማህበረሰብ ችግሮችን በተጨባጭ የመፍታት አቅም | 15 | |
| | በአካባቢ የሚገኙ ቁሳቁስና ሀብትን ጥቅም ላይ ከማዋል አንጻር | 10 | |
| | የአካባቢ ብክለትን የማያስከትልና ለጥበቃ ያለው አስተዋጽኦ | 8 | |
| | ለውድድር የቀረቡ የፈጠራ ስራዎች ብዛት | 12 | |
| 2 | ከትምህርት ጋር የተጣጣመ ተግባራዊና ውጤት ያለው ምርምር ማካሔድ | 12 | |
| | ምርምር በማካሄድ የተዘጋጀ ደረጃውን የጠበቀ ሰነድ | 5 | |

| | | | |
|---|---|---|---|
| | የምርምር ውጤቱን ለት/ቤቱ አካላትና ለሌሎች አቅርቦ ማስገምገም | 3 | |
| | የምርምር ውጤቱን ተግባራዊ በማድረግ ተጨባጭ ውጤት ማስገኘት | 4 | |
| 3 | **አጋዥ/ማጣቀሻ (የቤተ ሙከራ ማኑዋል፣ሞጁል ወዘተ) ማዘጋጀት** | 10 | |
| | የተዘጋጁ ደረጃቸውን የጠበቁ የማጣቀሻ መጻህፍት | 5 | |
| | የተዘጋጁ ሞጁሎች | 3 | |
| | ወቅታዊነትን የጠበቀ የቤተ ሙከራ ማኑዋል | 2 | |
| 4 | **ሽልማቱ በሚሰጥበት ዓመትና ከዚያ ቀደም ባለው አንድ ዓመት በትምህርት ማበልጸጊያ ማዕከል ወይም በሌላ ቦታ የተዘጋጀ ከሚያስተምረው ትምህርት ጋር ተያያዥ የሆነ የማስተማሪያ መርጃ መሳሪያ** | 10 | |
| 5 | **ንድፈ ሀሳብን ተግባራዊ ለማድረግ የቤተ ሙከራ አጠቃቀም** | 8 | |
| 6 | **ዕውቀት ፣ ክህሎትና የቋንቋ ችሎታ** | 5 | |
| | በሚያስተምረው ትምህርት ያለው ዕውቀት | 2 | |
| | የማስተማር ችሎታ | 2 | |
| | የቋንቋ ክህሎት | 1 | |
| 7 | **በትምህርት ቤቱ የሳይንስ ክበብ ያለው ተጨባጭ ተሳትፎ** | 5 | |
| | ክበቡን ለመምስረት ያደረገው ተጨባጭ ተሳትፎ | 1 | |
| | በክበቡ ያለው የማስተባበር ሚና | 2 | |
| | በክበቡ ያለው ንቁ ተሳትፎ | 2 | |
| 8 | **የተማሪዎች አያያዝና በት/ቤቱ የሚያሳየው አርአያነት** | 5 | |
| | ተገቢ የተማሪዎች አያያዝ የሚያደርግ መሆኑ | 3 | |
| | በት/ቤቱ የሚያሳየው አርአያነት | 2 | |
| | **የተወዳዳሪው የተጠቃለለ ውጤት ከ100 %** | | |

## አባሪ 7 የተወዳዳሪዎች የውል ስምምነት

1. አመልካቾች ማመልከቻቸውን ለውድድሩ ሲያስገቡ በማመልከቻቸው ውስጥ ስለተካተቱት መረጃዎች ኃላፊነት ይወስዳሉ።
2. አመልካቾች ያካተቷቸው ማብራሪያዎችና መረጃዎች እውነት ያልሆኑና የተሳሳተ መረጃ የሚያስተላልፉ ሆነው ከተገኙ የሽልማት ዳኞች ባላቸው ሙሉ የመወሰን ስልጣን መሰረት በማንኛውም የውድድሩ ደረጃና ወቅት አመልካቹን ወይም አመልካቾቹን ከውድድር ሊያስናብቱ ይችላሉ።
3. አመልካቾች በማመልከቻቸው ውስጥ የራሳቸውን የፈጠራ ስራ ብቻ በኢጋኘነት ማቅረብ ይኖርባቸዋል።
4. ሁሉም አመልካቾች በማመልከቻቸው ውስጥ ያሉ ሃሳቦችና ቁሳቁሶች የግልና የአዕምሮ ንብረት መብትን ጨምሮ የማንኛውም የሶስተኛ ወገን መብትን እንዲሁም የቅጅ መብትን፣ የንግድ ምልክትን፣ የፈጠራ መብትን ወይም በሌሎች በህግ የተጠበቁ መብቶችን የማይጥሱ መሆን አለባቸው። ነገር ግን በማመልከቻው ውስጥ የሶስተኛ ወገን የቅጅ መብት፣ የንግድ ምልክት ወይም ሌሎች የአዕምሮ መብቶችን የያዙ ቁሳቁሶች የተካተቱ ከሆነ ይህንን ለማድረግ የሚያስችል ህጋዊ ፈቃድ፣ የባለመብቱ ፈቃደኝነትና ነፃ ስለመሆናቸው አመልካቾች ኃላፊነትና ዋስትና ይወስዳሉ።
5. የሽልማት ዳኞች ማንኛውንም በአመልካቾች ይፋ የተደረገን፣ ማብራሪያ የተሰጠበትን ወይም ውይይት የተደረገበትን መረጃ በፎቶ ኮፒ፣ በፎቶ፣ በምስልና በድምፅ ቀርፀው ሊይዙ እስከቻሉ ድረስ አመልካቾች ለውድድር ባቀረቧቸው ፈጠራዎች የአዕምሮ ንብረት ባለመብትነታቸው የተጠበቀ ነው።
6. ቢሮው ስለተመረጡት ተወዳዳሪዎች ለህዝብ አንዳንድ መረጃዎችን እንዲሁም ፎቶ፣ የህይወት ታሪክ፣ የንግድ ዘርፍ፣ የድርጅት ዓርማ፣ የስራ ስኬት ባጭሩ የመሳሰሉትንና ስለተወዳደሩበት የፈጠራ ስራ ህዝብ በሚበዛባቸው አካባቢዎች በተለይም በድረ-ገፆቻቸው፣ በመፅሄቶቻቸው፣ በአጫጭር የፅሁፍ መግለጫዎቻቸው፣ በመደበኛ ሪፖርቶቻቸው ወዘተ የማውጣት መብት አለው።
7. ማመልከቻ ከማስገባትና በሚጠየቁበት ጊዜ ብቻ ተጨማሪ መረጃ ከማቅረብ ውጭ፣ አመልካቾች ወይም በአመልካቾች ስም ሌላ ሰው የውድድሩን ውጤት ለማስቀየር በማሰብ ማንኛውንም የሽልማት ዳኞች አባል እንዲሁም ተወካዮችን ማግኘት ወይም ለማግኘት መሞከር ከውድድር ያሰርዛል።
8. እያንዳንዱ ተወዳዳሪ የመወዳደሪያ ቁሳ ቁሶችን (materials) ለሽልማት ዳኞች ተደራሽ ማድረግ አለበት። ቢሮው በአመልካቾች ለቀረቡና ውይይት ለተደረገባቸው ፋይሎችና መረጃዎች ምንም አይነት በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ በምስጢር የመጠበቅ ዋስትና

አይሰጡም። የውድድር ዳኞችም ከውድድር ቁሳቁሶች (materials) ጋር በተያያዘ የምስጢር መጠበቅ ስምምነት አይፈርሙም።

9. ስለፈጠራው እርግጠኝነት በሚደረገው የመስክ ምልከታ ማረጋገጫ ሂደት አመልካቾች የማምረቻ ቦታቸውን ለሽልማት ዳኞች ክፍት ለማድረግ እንደ አግባቡም የፈጠራውን ናሙና ለማሳየት ተስማምተዋል።

10. የሽልማት አወሳሰዱ እዚህ በተመለከቱት የውድድር ህጎች፣ ሰነዶች እና ስምምነቶች ውስጥ የተዘረዘሩትን ሁሉንም መስፈርቶች የሽልማት ተቀባዩ በማሟላቱ ላይ የተወሰነ/የተመረኮዘ ነው።

እኔ________________________________________________ ከላይ የተዘረዘሩትን ግዴታዎች አንብቤ እና ተረድቼ በመመሪያው መሠረት ለመመራት መስማማቴን በእኔ እና/ወይም በወከልኳቸው ሰዎች ስም በፊርማዬ አረጋግጣለሁ።

ፊርማ፡- ________________ ቀን፡- ________________________

## አባሪ 8

## በማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል ሳይንስና ኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ቢሮ
## የሳይንስና ቴክኖሎጂ የፈጠራ ስራ ባለሙያዎች ውድድር የማመልከቻ ቅጽ

1. የግል መረጃ

- ስም ፡- ........................... የአባት ስም ፡- ............... የአያት ስም ፡- ................
- ፆታ ፡- ሴት ☐ ወንድ ☐
- አድራሻ
  - ስልክ ፡- ሞባይል ፡- ...................... መደበኛ ፡- ........................
  - ዞን ፡- ............... ከተማ ፡- .................. ወረዳ/ክ/ከተማ ፡- .........................
  - ፋክስ ፡- ........................ ኢ_ሜይል ፡- ........................

2. ትምህርትና የስራ ሁኔታ

- የሰለጠኑበት የሙያ መስመር ፡- ..................... የትምህርት ደረጃ ፡- ..................
- የሚሰሩበት ተቋም ፡- ......................... የስራ ድርሻ ፡- ............ የስራ ልምድ፡.........

3. ለመወዳደር የሚያመለክቱበትን የሳይንስና የቴክኖሎጂ ዘርፍ / እባክዎ የ"x" ያድርጉ /

- ቴክኖሎጂና ምህንድስና ☐
- የተፈጥሮ ሳይንስ ☐

- ግብርና ☐
- ህክምናና ጤና ሳይንስ ☐
- ዉሃ፣መስኖ፣ማዕድንና ኢነርጂ ☐
- ኢንዱስትሪ ☐

4. የምርምርና የፈጠራ ውጤቱ ርዕስ ፡- ..........................................................................

...............

5. **ስለ ፈጠራው የተሰጠ አጭር ማብራሪያ**

ሀ. ይህንን የፈጠራ ስራ ለመስራት በመነሻነት የተለየ ችግር/ፍላጎት ፡- ....................................................................................................................................................................................................................................................................................................................................................................................................................

ለ. የአሠራር ቅደም ተከተል ፡- ..................................................................................................................................................................................................................................................................................................................................................................................................

ሐ. የተግባራዊነት ወሠን ፡- .................................................................................................................................................................................................................................................................................................

መ. የፈጠራ ውጤቱ አሁን ጥቅም ላይ ካለው አሠራር አንጻር የሚያስገኘው የተለየ ፋይዳ፡- ......................................................................................................................................................................................................................................................................................................................................................................................................................................................................................

እኔ አመልካች .............................................. ከላይ የሰጠሁት መረጃ ትክክለኛ መሆኑን በፊርማዬ አረጋግጣለሁ፡፡

ፊርማ ፡- ..............................

ቀን ፡- ..............................